VICTORIA

Companion card™

Amharic
አማርኛ

# Cardholder Handbook

# ካርዱን ለያዘ ትገኘ የመረጃ መፅሐፍ




Community Support Fund Victoria

Victoria The Place To Be

# ካርዱን ለያዘ ትኀሽ የመረጃ መፅሐፍ

መስከረም/September 2003

በ Victorian Government Department of Human Services (ቪክቶሪያ መንግሥት የሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያ) ሜልበርን፣ ቪክቶሪያ በኩል የቀረበ ነው።
© Copyright State of Victoria, 2003.

በዚህ ፅሁፍ ላይ ያለውን ሰነድ ለመቀየር ወይም ለመጨመር እንደማይቻል ወይም መረጃው እንደማይሸጥ ወይም ያለአግባብ መጠቀም እንደማይቻል ነው።

የቪክቶሪያ መስተዳደር ሰነዱ እንደገና እንዲታተም ቢፈቅድም ትክክለኛ መሆን እንዳለበትና ለሚደረገው የፅሁፍ ቅጅ የቪክቶሪያ መስተዳደር ዋና ባለቤቱ ለመሆኑ ማሳወቅ ይገባል።

Companion Card (የአብሮ ተጓዥ ካርድ) በቪክቶሪያ መስተዳደር የንግድ ምልክት ይሆናል።

በበለጠ መረጃና ስለ የቪክቶሪያየCompanion Card ካርድ ትኀሽ የመረጃ መፅሐፍ ለማግኘት በሚከተለው ዌብሳይት ላይ ይገኛል:

**www.companioncard.org.au**

ወይም በስልክ lCompanion Card መረጃ መስመር በሚከተለው መደወል:

**1800 650 611**



# ርዕሰ ማውጫ


| | |
|---|---|
| ስለዚህ ትኀሽ የመረጃ መፅሐፍ | 4 |
| የቃላት አገላለፅ | 4 |
| Companion Card ካርድ ለምን ተቋቋመ? | 5 |
| Companion Card ካርድ ምን'ድ ነው? | 6 |
| ካርዱን እንዴት መጠቀም እንደሚኖርብኝ? | 6 |
| አብሮ ተጓዥ (Companion) ምን ማለት ነው? | 6 |
| Companion Card ካርድ የት ላይ ነው መጠቀም የምችለው? | 7 |
| ምን ያህል ያስከፍላል? | 7 |
| ማን ማመልከት ይችላል? | 8 |
| ቋሚ የሆነ አካለ ስንኩልነት እንዳለብኝ እንዴት አውቃለሁ? | 8 |
| Companion Card ካርድ ስለማግኘት እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ? | 9 |
| Companion Card ካርድ ለማግኘት መስፈርቱን የማላሟላ ከሆነስ? | 9 |
| Companion Cards ካርዶችን ስለማደስ | 9 |
| Companion Card ካርዶችን ያለአግባብ ስለመጠቀም | 10 |
| ክስ/ቅሬታ ስለማቅረብ Complaints | 10 |
| ስለ ካርዶች መተካት | 11 |
| አድራሻ ስለመቀየር | 11 |
| ስለ Companion Card ካርድ በበለጠ መረጃ ስለማግኘት | 11 |
| - በCompanion Card ካርድ ዌብሳይት | 11 |
| - ስለ Companion Card ካርድ የመረጃ መስመር | 11 |
| - በብዙ ቋንቋ የመረጃ መስመር በኩል እንዴት የCompanion Card ካርድ መስመርን ማግኘት እንደሚችሉ | 12 |
| ካርዱን ለያዙ የማመልከቻ ቅጹን ለማጠናቀቅ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች | 12 |
| ካርዱን ለያዘ ስያሜና ሁኔታዎች | 16 |
| ተጨማሪ ምንጮች | 17 |
| - ስሌሎች የአካለ ስንኩል አገልግሎት ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት | 17 |
| - በአካለ ስንኩል ላይ አድልዎ መፍጠርና ስለ መብትዎ በበለጠ መረጃ ለማግኘት | 17 |
| Privacy (ለብቻነት) | 19 |

# ስለዚህ ትንሽ የመረጃ መፅሐፍ

Companion Card (የአብሮ ተጓኙ ካርድ) ፕሮግራም በዚህ ትንሽ የመረጃ መፅሐፍ ለርስዎ እንዴት እንደሚረዳ ለማስረዳት ተብሎ የተዘጋጀ ይሆናል። የአብሮ ተጓኙ ካርድ ለማመልከተ ከወሰኑ ይህ ሊረዳዎት ይችላል።

የ Companion Card ከያዙ ያለዎትን መብትና ኃላፊነት ዝርዝር ሁኔታ በዚህ ትንሽ መፅሐፍ ውስጥ ይቀርባል። በተጨማሪም እንዴት የማመልከቻ ቅጽና ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት እንደሚችሉ በዚህ መፅሐፍ የተገለጸ ሲሆን እርስዎን ሊረዱ የሚችሉ ሌሎች ምንጮችም ዝርዝር ይቀርባል።

የማመልከቻ ቅጹን ከማጠናቀቅዎ በፊት ይህንን ትንሽ የመረጃ መፅሐፍ ማንበብ አለብዎ። የተጠየቀው ዝርዝር መረጃ በማመልከቻ ቅጹ ላይ "ለመሙላት የተጠየቀ በሚለው ካርድ ለሚይዙ የማመልከቻ ቅጽ" ክፍል ላይ የተካተተ ይሆናል። እንዲሁም የማመልከቻ ቅጹ ከዚህ ትንሽ የመረጃ መፅሐፍ ጋር አብሮ የተካተተ ይሆናል። ምናልባት ይህን መፅሐፍ ቆይተው ለማንበብና ማየት ከፈለጉ ከርስዎ ጋር መያዙ ይደገፋል።

**የቃላት አገላለፅ**

**"Cardholder/ካርድ የያዘ" –** አካለ ሰንኩል ለሆነ ማገኛውም ሰው ሲሆን ይህም በዕድሜና በስነ-አእምሮ በሚከሰተ በሽታ ችግር ያለባቸውን ሲያካተት Companion Card ካርድ እንደሚፈቀድና የአብሮ ተጓዡ ፎቶግራፉና ዝርዝር ሁኔታቸው በካርዱ ላይ እንደሚታይ ነው።

**"Companion/አብሮ ተጓኙ"** – ይህ ፕሮግራም "አብሮ ተጓኙ" ለሚለው ቃል የሚከፈልበት ወይም የማይከፈልበት እርዳታ ለመሆኑ ለመግለፅ ይጠቀማል ወይም ካርዱን ለያዘው እንክብካቤ ሰው በማህበረሰብ ለሚካሄድ እንቅስቃሴ አብሮ ለመሄድ እንዲፈቀድለትና ተሳትፎ እንዲያደርግ እንዲያስችል ይሆናል።

**"Affiliate/ግንኙነት ያለው"** – የዚህ ጥቅም ለCompanion Card ካርድ ተቀባይነት በመስጠት የተመዘገቡትን ድርጅቶች፣ ንግዶችና የመግቢያ ዋጋ ወይም ለተሳትፎ የሚያስከፍሉ አገልግሎቶች ይገልጻሉ። በቪክቶሪያ ውስጥ ለተመሠረቱ ፋብሪካዎች ማለት በአገር አቀፍ ለሚሠሩ ወይም ለተቋቋሙ ግንኙነት ማድረግ ይፈቀድላቸዋል።

**"Companion Ticket/ለአብሮ ተጓኙ ትኬት" –** Companion Card ካርድ ከያዘው ሰው ጋር ወደ እንቅስቃሴ ቦታ አብሮ የሚገባ ካስፈለገ ያለምንም ክፍያ ይህ ተጨማሪ ቲኬት ለአብሮ ተጓኙ ይሰጣል።



## Companion Card ካርድ ለምን ተቋቋመ?

The Victorian Network On Recreation and Disability (በቪክቶሪያ ለአካለ ስንኩል መዝናኛ የአሠራር መዋቅር) አካለ ስንከኩላን የሚፈልጉትን ለማሟላት ሲባል ስለ Companion Card ካርድ ሃሳብ በማፍለቅ የዋጋ ፖሊሲ በመተመን ብዙ የመዝናኛ እንቅስቃሴ መንገዶችን ያለምንም አድልዎ እንዲቀርብ ተደርጓል።

በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ለመሳተፍ የሚፈልጉ አካለ ስንኩላን በማህበረሰቡ ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ እኩል መብት እንዳላቸው ነው። ይህ ቀዳሚ መብት በእኩልነት መብትና የአካለ ስንኩል አድልዎ መፍጠር ክፍል አንቀጽ ቁጥር 42 of the Equal Opportunity Act 1995 (Vic) እና Section 8 of the Disability Discrimination Act 1992 (Cwlth) መሠረተ የተጠበቀ ይሆናል። የአብሮ ተጓኙ እርዳታ ለሚያስፈልገው ሰው መቃወም በነዚህ አንቀጾች መሠረት እንደ ህገ-ወጥነት ያስቆጥራል።

ቀደም ሲል አንድ አካለ ስንኩል በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ተሳትፎ ሲያደርግ የአብሮ ተጓኙ እርዳታ ካስፈለገው አንዳንዴ ሁለት ዓይነት የመግቢያ ክፍያዎች ማለት ለራሳቸውና ለአብሮ ተጓዡ ይከፍሉ እንደነበረ ነው።

ይህ አሰራር አድልዎን ይፈጥራል ምክንያቱም ለአካለ ስንኩል ለሆነ ሰው ሁለት ጊዜ የመግቢያ ክፍያ ያካሂዳል ማለት ነው።

ይህን አግባብ ያልሆነ ክፍያ በብዙ የእንቅስቃሴ ቦታዎች በመነገሩ ለአብሮ ተጓኙ ሰው የነፃ መግቢያ ፍቃድ እንደተሰጠ ነው። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ ማን የአብሮ ተጓኙ ፍቃድ ማግኘት እንደሚችል በነዚህ ድርጅቶች ቀላልና ቀጣይ የሆነ መለያ ዘዴ እንደሌላቸው ነው።

በአሁኑ ጊዜ የአካለ ስንኩላንን መብት ለማበረታታት የ Companion Card ካርድ ላላቸው ትኬት በደህና ዋጋ ይሰጣል። ይህ በቅናሽ ለመግዛት የምትጠቀምበት ካርድ አይደለም።

የአብሮ ተጓኙ አስፈላጊነት በቀላሉ መንገድ ለማሳወቅ Companion Card ካርዱ ሲሆን ፀረ-አድልዎ ህግን በተመለከተ ኢንዱስትሪው መከተል ያለበትን እንዲያውቅ ይረዳል።

የ Companion Card ካርድ የማትረፊያ ፕሮግራም አይደለም። ለአስተዳደር ፕሮግራም የሚውለው የገንዘብ ወ በቪክቶሪያ መንግሥት፣ የማሕበረሰብ እርዳታ ዘዴ ቀስቃሽ አማካኝነት ይሰጣል።






## Companion Card ካርድ ምን'ድ ነው?

ይህ ካርድ የገንዘብ ቦርሳ መጠን ያለው ካርድ ሲሆን በዕድሜ ወይም የስነ-አእምሮ ህመምተኛ ለሆነ አካለ ስንኩል ይሰጣል። በእንቅስቃሴ ቦታ ላይ የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ለሚያስፈልገውና ካርዱን ለሚይዘው ሰው ፎቶግራፍና ማንነቱን የሚገልፅ ይሆናል።

በአሁኑ ጊዜ ሰዎች በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ቦታ ለመሳተፍ ተጨማሪ ክፍያ ላለመክፈል የሚኖሩቸው መብት በ Companion Card ካርድ በኩል የተሻለ እንደሚሆን ነው ምክንያቱም አብሮ ተጓዥ እርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ይሆናል። ይህ አሠራር የቅናሽ ዋጋ ዘዴ አይደለም ወይም አካለ ስንኩላን ሌላ ነገር ሲገዙ በቅናሽ ማግኘት የማይችሉትን በዚህ ካርድ ያገኛሉ ማለት አይደለም።

## ካርዱን እንዴት መጠቀም እንደሚኖርብኝ?

ቦታ ሲያስይዙ ወይም ትኬት ሲገዙ ያብሮ ተጓዥ ካርዱን በማሳየት ካርዱን የያዘው ሰው የሚረዳ ሰው ካስፈለገው በተጠየቀው የእንቅስቃሴ ቦታ ላይ አብሮ መግባቱን ለማረጋገጥ ይሆናል። "affiliate" (ተሳታፊ) የሆኑ ድርጅቶች ለ Companion Card ካርድ ተቀባይነት በመስጠት ካርዱን ለያዘ ሰው ሁለተኛ ትኬት ያለክፍያ ይሰጣል።

ካርዱን የያዙ ሰዎች በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ ያለ አብሮ ተጓዥ እርዳታ ተሳትፎ ካደረጉ የራሳቸውን ካርድ ብቻ በመጠቀም Companion Card Ticket (የአብሮ ተጓዥ ትኬት) ያገኛሉ።

የ Companion Card ካርድ ውጤታማና ሊስፋፋ የሚችለው በሁለቱም ማለት ካርድ በያዙትና በተሳታፊ (affiliates) ድርጅቶች በሚኖራቸው ጥሩ አድራጎት ይሆናል። የአብሮ ተጓዥ እርዳታ በማያስፈልግበት ጊዜ የ Companion Card ካርዱን ለመጠቀም ከሞከረ ኢንዱስትሪው በፕሮግራሙ ላይ ለመሳተፍ የሚኖረውን በጎ ፍላጎት እንደሚያበላሽ ይሆናል.

## አብሮ ተጓዥ (Companion) ምን ማለት ነው?

አብሮ ተጓዥ ሰው ሲሆን እንቅስቃሴ በሚደረግበት ቦታ ላይ እንዲረዳው ካርዱን በያዘ ሰው የሚመረጥ ይሆናል። አብሮ ተጓዡ የሚከፈለው ወይም የማይከፈለው ረዳት እንክብካቤ ሰ ሊሆን ይችላል። ከነርሱ ጋር ማን አብሮ ተጓዥ እንደሚሆን ካርዱ ያላቸው ሰዎች እራሳቸው ሲመርጡ እንደ እንቅስቃሴው ዓይነትና ሁኔታ ሊለያይ ይችላል።

አንድ ሰው ካርድ ከያዘ ጋር ለማህበራዊ ወይም ለመዝናናት ሲባል ከሄደና በእንቅስቃሴ ቦታው ላይ የሚጠበቅበትን እርዳታ ካልሰጠ አብሮ ተጓዥ ሊያሰኘው አይችልም።



## Companion Card ካርድ የት ላይ ነው መጠቀም የምችለው?

ተሳታፊ (affiliates) ድርጅቶች፤ የንግድና የምርት መሸጪ ሱቅ የመግቢያ ክፍያ ወይም የተሳትፎ ክፍያ ሊያስከፍሉ ሲችሉ በCompanion Card ካርድ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ በግልፅ መመዝገብ ይኖርባቸዋል። በቪክቶሪያ ውስጥ በተመሰረተ ኢንዱስትሪ ማለት በአገር አቀፍ ለሚሠሩ ወይም የምርት ማቅረቢያ ሱቆች ተሳታፊ ለመሆን ይፈቀድላቸዋል።

የCompanion Card ካርድ ፕሮግራም በቪክቶሪያ አነሳሽነት የተመሠረተና በቪክቶሪያ መዝናኛ፤ በማዝናኒያ ቦታ፤ በማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴ ቦታዎች ላይ በማተኮር የተቋቋመ ፕሮግራም ይሆናል። እንዲሁም ሌሎች ኢንዱስትሪዎች በፕሮግራሙ ውስጥ ለመሳተፍ ይፈልጉ ይሆናል። በተሳታፊ የንግድ ተቋም መግቢያ ላይ በተለጠፈ የተለያዩ የአብሮ ተጓዥ አርማዎች ወይም በሚያወጡት የማስታወቂያ ማስረጃዎች ላይ ማየት ይሆናል።

Companion card
Accepted Here

አንዳንድ የእንቅስቃሴ አስተባባሪዎች ስለ Companion Card ካርድ [ማስታወቂያ አለመለጠፍ] ላያውቁ ይችላሉ ነገር ግን ካሳዩያቸው ወይም ከነገሩዋቸው ሃሳቡን ሊቀበሉት ይችሉ ይሆናል። በካርድዎ ጀርባ ላይ በዌብሳይት የእንቅስቃሴ አስተባባሪዎችን አድራሻና ቴሌፎን ቁጥር በማቅረብ ስለ Companion Card ካርድ መረጃና እንዴት በፕሮግራሙ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚቻል ያቀርባል። ይህንን መንገድ በማወቅ ብዙ ኢንዱስትሪዎችና ድርጅቶች በፕሮግራሙ ላይ እንደሚሳተፉና የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች መብታቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል።

## ምን ያህል ያስከፍላል?

በቪክቶሪያ መስተዳድር ግዛት ለማህበረሰብ አበረታች ዘዴ በሚቀርብ የገንዘብ እርዳታ በኩል የCompanion Card ካርድ በነፃ የሚከፈል ይሆናል።



## ማን ማመልከት ይችላል?

(በቪክቶሪያ ሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያ) Victorian Department of Human Services ለአካለ ስንኩላን አገልግሎት አንቀጽ/Disability Services Act 1991 (Vic) መሰረት የCompanion Card ካርድ አመልካቾች የመመዘኛ ነጥቦች ማሟላት ይኖርባቸዋል።

በጥቅሉ ለካርድ ማመልከት የሚቻለው:

1. ከዕድሜና ከስነ-አእምሮ ሕመም ጋር በተያያዘ የአካለ ስንኩል ከሆኑ
2. ቋሚ የአካለ ስንኩልነት ካለዎት – ወይም ወደ ቋሚነት የሚያመራ ከሆነ
3. በማህበራዊ እንቅስቃሴ ቦታ ሲሄዱ የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ካስፈለግዎ
4. የአውስትራሊያ ነዋሪ ከሆኑ ወይም አውስትራሊያ ለመኖር ጊዜው ያላለፈበት ቪዛ ካለዎት፤
5. ማመልከቻዎና ፎቶግራፍዎ አግባብ ላለው ባለሙያ ከተፈረመበት

የCompanion Card ካርድ ሲያመለክቱ የገቢ መንጭ ወይም የንብረት መጠን ግምት ውስጥ አይገባም እንዲሁም ሰዎች በሥራቸው ወይም የተወለዱበት አገር ምክንያት አይሆንም።

Companion Card ካርድ ለማመልከት የዕድሜ ገደብ የለውም ነገር ግን ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች ሲያመለክቱ በወላጆቻቸው ወይም ህጋዊ የሆነ አሳዳጊ መፈረም ይኖርበታል።

አገልግሎት ሰ ድርጅቶች ወይም ለወደፊት አብሮ ተጓዥ የየ Companion Card ካርድ ለማመልከትላይፈቀድላቸው ይችላል። ካርዶችን መሰጠት እንጂ ንብረትነቱ ችግር ላለው የአካለ ስንኩል ሰው ብቻ ይሆናል። ይህም ካርዱን ለያዙ ሰዎች በእንክስቃሴ ቦታ ላይ ማን አብሮ መጓዝ እንደሚችል መምረጥ ያስችላቸዋል።

ወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ ካልሆኑ በስተቀር ያለምንም የፅሁፍ ስምምነት አመልካችን ወክሎ ማመልከቻ ማቅረብ አይቻልም።

## ቋሚ የሆነ አካለ ስንኩልነት እንዳለብኝ እንዴት አውቃለሁ?

ምንም እንዐን ችግሩ በየጊዜው ቢቀያየርም በቀሪ ሕይወት ላይ የቋሚ አካለ ስንኩልነት ለመኖሩ ያረጋገጡ ይሆናሉ።

ምንም እንኳን ችግሩ ለብዙ ጊዜ ቢቆይም በቀሪ ሕይወትዎ ላይ አካለ ስንኩልነት የማይቀጥል ከሆነ እንደ ቋሚ አካለ ስንኩልነት አይቆጠርም።






## Companion Card ካርድ ስለማግኘት እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?

Companion Card ካርድ እንደሚያስፈልግዎ በሚከተሉት ሁለት መንገዶች ማረጋገጥ ይቻላል፤

1. በካረድ ለያዙ በሚያቀርቡት ማመልከቻ ቅጽ ላይ ከተዘረዘሩት እርዳታ ወይም አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ የሚያገኙ ከሆነ። እነዚህን እርዳታዎች ወይም አገልግሎቶች ቀደም ብለው ለሚያገኙ ሰዎች የCompanion Card ካርድ ለማስፈለጉ የሚያረጋግጥ ግምገማ ማካሄድ።

ወይም

2. በሚከተሉት የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ተሳትፎ ለማድረግ የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ለምን እንዳስፈለግዎ ሊነግሩን ይችላሉ፡
- ግንኙነት ለመፍጠር
- ለመማር/እቅድ ለማውጣት/ለማሰብ
- ለመዘዋወር
- እራስን ለመንከባከብ

## Companion Card ካርድ ለማግኘት መስፈርቱን የማላሟላ ከሆነስ?

Companion Card ካርድ የሚሰጠው ለፕሮግራሙ የወጡትን መመዘኛ ነጥቦች ያሟላ ሰው ብቻ ይሆናል። አንድ ሰው የአብሮ ተጓዥ እርዳታ የሚያስፈልግበት ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ ነገር ግን Companion Card ካርድ ለማግኘት አይፈቀድለትም። ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ጊዚያዊ የአካል መሰናከል ችግር ከደረሰበት። እንደ ሁኔታው ግለሰብና የእንቅስቃሴ ቦታ አስተባባሪዎች በመደራደር Companion Ticket ትኬት ያስፈለገበትን በመግለፅ አማራጭ ዘዴን ይፈልጋሉ።

## Companion Cards ካርዶችን ስለማደስ

Companion Card ካርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት ያገለግላል። ከዚህ ጊዜ በኃላ ካርዱ ያላቸው ሰዎች በሞላ ማሳደስ ይኖርባቸዋል። የማደሻው ጊዜ የሚወሰነው -

- ሕይወት በአካል እስካለች ድረስ (ካርዱ በእርጅና ሲቀደድ);
- ካርዱን ለያዙ ፎቶግራፋቸው ሁልጊዜ መታየት ሲገባው፡
- ካርዱ ያላቸው አንዳንድ ሰዎች የሚያስፈልጋቸው እርዳታ መለወጥ ሲያስፈልግ።

ካርዱን ለማደስ አዲስ የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ወደ Companion Card ካርድ ፕሮግራም ማቅረብ ያስፈልጋል።

በወቅቱ የተያዘው ካርድ የሚያበቀቃበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት ለስድስት ወር የሚሆን ለማሳደስ ማመልከት ይቻላል።

## Companion Card ካርዶችን ያለአግባብ ስለመጠቀም

ጠንከር ባለ የማመልከቻ አሰራር ካርዱን ያለአግባብ በመጠቀሙ መንገድ የቀነሰ ሲሆን Companion Card ካርድ ወደሚፈለገው ቡድን እንዲደርስ ይደረጋል።

ካርዱ ሲነደፍ ብዙ ጥንቃቄዎችን በሚያንፀባርቅ መልኩ ነው። ተሳታፊ የሆኑ ድርጅቶች ምዝገባ በሚያደርጉበትና የመግቢያ ትኬቱን በሚያሰራጩበት ጊዜ ካርዱን ለያዙ ሰዎች ማንነታቸውን ለመለየት እንዲጠቅማቸው ይሆናል። ካርዱን የያዙ አላግባብ ለመጠቀም ከሞከሩ ውጤቱ ካርዱ መሰረዝ ይሆናል።

Companion Card ካርድ ውጤታማና ሊስፋፋ የሚችለው በሁለቱም ማለት ካርድ በያዙትና በተሳታፊ (Affliates) ድርጅቶች በሚኖራቸው ጥሩ አድራጎት ይሆናል። ካርድ ለያዙ ሰዎች በሆነ የእንቅስቃሴ ቦታ ከአብሮ ተጓዝ ረዳት ጋር ለመግባት ሲፈልጉ ብቻ ካርዱን እንዲያሳዩ ይጠየቃሉ። የአብሮ ተጓዥ እርዳታ በማያስፈልግበት ጊዜ Companion Card ካርዱን ለመጠቀም ከሞከሩ ውጤቱ መሰረዝና በኢንዱስትሪው ፕሮግራም ላይ እንዳይሳተፋ ይደረጋል። ይህም ለሌሎች ሰዎች የሚሰጠውን ፕሮግራም ስጋት ላይ ሊጥለው ይችላል።

## ክስ/ቅሬታ ስለማቅረብ Complaints

ስለ Companion Card ካርድዎ ተቀባይነት አለማግኘት ወይም በእንክስቃሴ ቦታ ላይ በአግባብ አለመስተናገድ ቅሬታ ካልዎ በመጀመሪያ በእንቅስቃሴው የአስተዳደር አያያዝ በኩል ጉዳዩ እንዲፈታ ይሞክሩ። በእንቅስቀቃሴ አስተዳደር የሚሰጥዎ መልስ የማያረካዎ ከሆነ በዚህ ትንሽ መፅሐፍ ውስጥ "Additional Resources" ስር የተዘረዘሩትን የእርዳታ ወኪሎች ማናገር ይሆናል።

<u>ስለ Companion Card ካርድ ባቀረቡት ማመልከቻ በተሰጠው መልስ</u> ላይ ቅሬታ ካለዎ በአብሮ ተጓዥ ካርድ ፕሮግራም ላይ ክስ መመሥረት ይችላሉ። ይህንን እንዴት ማቅረብ እንደሚችሉ በCompanion Card ካርድ ቴሌፎን መረጃ ማቅረቢያ መስመር ዝርዝሩን መጠየቅ ነው።






## ስለ ካርዶች መተካት

ካርድዎ እንዲተካ ለመጠየቅ የሚችሉት -

- Companion Card ካርድዎ ከጠፋ፤
- Companion Card ካርድዎ ከተሰረቀ ወይም ሲበላሽ
- ስምዎን ሲቀይሩ፤
- ፎቶግራፍዎ መታደስ ሲያስፈልግ

ካርዱ እንዲለወጥ ለመጠየቅ የመቀየሪያ ቅጹን ዝርዝር መለወጥና ለCompanion Card ካርድ ፕሮግራም ማስገባት።

## አድራሻ ስለመቀየር

የመላኪያ አድራሻዎን ለመቀየር ከፈለጉ ለCompanion Card ካርድ ፕሮግራም በምትኩ ለማግኘት ዝርዝሩን በቅጹ ላይ በመሙላት ማቅረብ።

ካርዱን ለመተካት / የቅጹን ይዘት ለመለወጥ የዌብሳይታችንን መጎብኘት ወይም በቴሌፎን የCompanion Card ካርድ መረጃ መስመር ቅጹ እንዲላክላችሁ መጠየቅ።

## ስለ Companion Card ካርድ በበለጠ መረጃ ስለማግኘት

### በCompanion Card ካርድ ዌብሳይት

**www.companioncard.org.au**

በዚህ ዌብሳይት ላይ ስለ የCompanion Card ካርድ ፕሮግራም፤ ቁልፍ በሆኑ የመረጃ የፅሁፍ ትርጉም፤ ለጥያቄ መልስ እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ የዌብሳይት መገናኛ የተለያዩ መረጃዎች ቀርበዋል።

የተተረጎመ የመረጃ ትንሽ መፅሐፍ፤ በእንግሊዝኛ የማመልከቻ ቅጽና የተለያዩ ሌሎች የCompanion Card ካርድ ቅጾች በዌብሳይቱ ላይ ሊገኝ ይችላል።

### ስለ Companion Card ካርድ የመረጃ መስመር

ማሳሰቢያ: ስለ Companion Card ካርድ ቀጥተኛ የሆነ ጥያቄ ካለዎ በCompanion Card ካርድ መረጃ መስመር በኩል እርዳታ ማጉኘት ይቻላል።

Companion Card ካርድ መረጃ መስመር ሠራተኛ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጠው በሥራ ሰዓት ሲሆን ስለ ካርዱ ፕሮግራምና በማመልከቻ ቅጹ ላይ ጥያቄ ካለዎት ይረዳል።

የዚህ ትንሽ የመረጃ መፅሐፍ ትርጉም ቅጅው፤ በእንግሊዝኛ የማመልከቻ ቅጽ እንዲሁም የተለያዩ ሌሎች Companion Card ካርድ ቅጾች የመረጃ ማቅረቢያ መስመሩን በማናገር ማግኘት ይቻላል።

ስልክ ቁጥር 1800 650 611 (እንግሊዝኛ ለሚናገር)

እንግሊዝኛ የማይናገሩ ከሆነ በብዙ ቋንቋ የመረጃ መስመር በኩል በአስተርጓሚ እርዳታ ከCompanion Card ካርድ የመረጃ መስመር ጋር ያገናኝዎታል (በብዙ ቋንቋ የመረጃ ማቅረቢያ መስመር በኩል እንዴት የአብሮ ተጓዥ ካርድ መስመርን ማግኘት እንደሚችሉ ማየት)።

## በብዙ ቋንቋ የመረጃ መስመር በኩል እንዴት የCompanion Card ካርድ መስመርን ማግኘት እንደሚችሉ

ስለ Companion Card ካርድ በተቀዱ መረጃዎች በቀን 24 ሰዓት በብዙ ቋንቋ የመረጃ መስመር በኩል ማብራሪያ ይቀርባል። እንዲሁም ጥሪ ለሚያደርጉ ሰዎች ከCompanion Card ካርድ መረጃ ማቀረቢያ መስመር ጋር እንዲነጋገሩ በሥራ ሰዓት አስተርጓሚዎችን ያቀናጃል።

| በብዙ ቋንቋ የመረጃ ማቀረቢያ መስመር የቴሌፎን ቁጥር | |
|---|---|
| አማርኛ | 1300 305 601 |
| አረብኛ | 1300 305 602 |
| ካንታኒስ | 1300 305 603 |
| ክሮሽያን | 1300 305 604 |
| ግሪክ | 1300 305 607 |
| ጣሊያነኛ | 1300 305 608 |
| ማሶዶኒያ | 1300 305 609 |
| ማንዳሪን | 1300 305 610 |
| ፖሊሽ | 1300 305 612 |
| የራሺያ | 1300 305 613 |
| የሰርቢያ | 1300 305 614 |
| ሱማልኛ | 1300 305 615 |
| የስፓኒሽ | 1300 305 616 |
| የቱርክ | 1300 305 617 |
| የቬትናም | 1300 305 618 |
| ሌሎች ቋንቋዎች | 1300 305 619 |



## ካርዱን ለያዙ የማመልከቻ ቅጹን ለማጠናቀቅ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች

### ማመልከቻ ለማቀረብ የሚወሰድ እርምጃዎች፤

**እርምጃ 1**: ይህን ካርድ ላለው ትንሽ መፅሐፍ ማንበብ።

**እርምጃ 2:** በእንግሊዝኛ ማመልከቻ ቅጹን መሙላት። በማመልከቻው ቅጽ ላይ ፎቶግራፍ መካተት ይችላሉ።

**እርምጃ 3:** ሁለት ጥራት የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፎችን ማዘጋጀት።

**እርምጃ 4:** በማመልከቻው ቅጽና በፎቶ ግራፎቹ ላይ በጤና ባለሙያ በኩል ማስፈረም፡ ባለሙያው በአገልግሎት አቀራቢ " Professional Declarations" በሚለው ስር ተገልጿል።

**እርምጃ 5:** የማመልከቻ ቅጹን በቀረበው ኢንቨሎፕ (ወይም በማንኛውም C4 sized መጠን በሆነ ኢንቨሎፕ) አድርገ ለሚከተለው መመለስ።፤

Companion Card Applications
Locked Bag 3014,
Hawthorn VIC 3122.

- ትክክለኛ የመላኪያ ፖስታ ማያያዝ
- የማመልከቻ ቅጹን አለማጠፍ
- ተጨማሪ ገጾች አለማያያዝ
- ዋናው ማመልከቻና ፎቶግራፎች በምንም ጉዳይ አይመለሱም
- ያልተሟላ ማመልከቻ ማለት ፊርማ የሌላቸው ወይም ያልተፈረመበት ፎቶግራፍ ተቀባይነት አይኖራቸውም።

### አጠቃላይ መረጃ

በማመልከቻዎ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰዎች ትክክለኛ የሆነ መረጃ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።

እባክዎ ያስተውሉ፡ በማመልከቻ ቅጹ ላይ የውሸት መረጃ ካቀረቡ ያስቀጣል።

ማመልከቻው መቅረብ ያለበት በአካለስንኩሉ ስም ሲሆን በCompanion Card ወይም ድርጅት ስም አይደለም። እያንዳንዱ የራሱ የሆነ የማመልከቻ ቅጽ መሙላት ይኖርበታል።

በማመልከቻ ቅጹ ላይ ያቀረቡት መረጃ ትክክለኛ ለመሆኑ በባለሙያ ፊርማ ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። በርስዎ በኩል ከተቀናጀ የማመልከቻ ቅጹን ከፎቶግራፎች ጋር በማያያዝ ወደ ባለሙያው በፖስታ መላክ ይችላሉ።

### ፎቶግራፎች

ሁለት ለመታወቂያ የሚሆን የፓስፖርት መጠን ያለው ከለርድ ፎቶግራፎች ከማመልከቻው ጋር በማያያዝ ማቀረብ ይኖርብዎታል።

በCompanion Card ካርድዎ ላይ የርስዎ ፎቶግራፍ ስለሚታተም እባክዎ ፎቶግራፉ ጥራት እንዲኖረውና ወቅታዊ ለመሆኑ ያረጋግጡ።

ፎቶግራፉን ከማመልከቻው ጋር በወረቀት ማያያዣ ማድረግ ያስፈልግዎታል። የወረቀት ማጣበቂያ፤ ማያያዣ ሽቦ ፈሳሽ ማጣበቂያ ወይም እስፒል አለመጠቀም ነው።

በእያንዳንዱ የፎቶግራፍ ጀርባ ላይ መጠቀስ ያለበት፤

ሀ) በፎቶግራፉ ላይ ያለው ሰው ስም እና፡

ለ) በማመልከቻ ቅጹ ላይ የፈረመው የአንድ ዓይነት ባለሙያ ፊርማ

ለፎቶግራፍ ወይም ከሰነዱ ጋር በተያያዘ ለተከፈለ ወጪ በCompanion Card ካርድ ፕሮግራም ተመላሽ አይሆንም።

### ለማመልከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- አዲስ ማመልከቻ ከሆነ ወይም ጊዜው ያበቃለት ካርድ ለማሳደስ ከሆነ የሚጠየቅ ዝርዝር ሁኔታ ይኖራል። ማመልከቻው ጊዜው ላበቃለት ካርድ ለማሳደስ ከሆነ የካርዱን ቁጥር መስጠት ያስፈልጋል።
- የርስዎን ግላዊ የሆነ ዝርዝር ሁኔታ የሚጠይቅ ክፍል ይኖራል። ይህም የርስዎን ስም፤ አድራሻ የትውልድ ቀን እና እርስዎ የሚገኙበትን ዝርዝር።
- የትኛው ሳጥን በበለጠ የርስዎን አካለስንኩልነት እንደሚገልፅ የሚል ክፍል ይኖራል። በአንዳንድ ምሳሌዎች የአካለሰንኩልነት ሁኔታዎች ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ። እንዲሁም የርስዎ ትክክለኛ ችግር ወይም ሁኔታ ማከረብ ያስፈልጋል። መደበኛ የሆነ የምርመራ ውጤት ችግር ከሌለብዎ የርስዎን ሁኔታ በአጭሩ መግለፅ አለብዎ።
- የርስዎ አካለስንኩልነት ዘላቂ ወይም ወደ ቋሚነት የሚያመራ ከሆነ ማሳወቅ አስፈላጊ ይሆናል። የርስዎ አካለስንኩልነት ዘላቂ ካልሆነ Companion Card ካርድ ለማግኘት የሚያስፈልገውን ነጥብ ላያሟሉ ይችላል። እባክዎ "Companion Card ካርድ ለማግኘት ካልቻልኩኝ" የሚለውን ክፍል በዚህ ትንሽ የመረጃ መፅሐፍ ውስጥ ስለ ድርጊቶችና መንገዶች ለበለጠ ማብራሪያ መመልከት ይሆናል።
- በዝርዝሩ ላይ ያሉትን ማንኛውም አገልግሎት ወይም እርዳታ የሚያገኙ ከሆነ የሚጠይቅ ሁኔታ እንዳለ ነው።
- በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ተሳትፎ በሚያደርጉበት ጊዜ የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ለምን እንዳስፈለግዎ የሚጠይቅ ክፍል ይኖራል

  ግንኙነት ለመፍጠር

  ለመማር/እቅድ ለማውጣት/ለማሰብ

  ለመዘዋወር

  እራስን ለመንከባከብ

## ትርጉም፡

**ግንኙነት ለመፍጠር:፡** ከሌሎች ጋር መረዳዳት ማለት ይሆናል። የአካስንኩልነትዎ በግንኙነት ላይ ችግር የሚፈጥርብዎ ከሆነ በህዝብ ድርጊቶች ላይ ያለ እርዳታ ለመገኘት ችግር ሊሆንብዎ ይችላል ምክንያቱም በማህበራዊ፣ በፀባይና በስሜታዊ ላይ ችግር ሊፈጠር ስለሚችል ነው። ከአብሮ ተጓዥ እርዳታ ሊያስፈልግዎ ይችላል ይህም ምግብ ለማዘዝ፣ ትኬት ለመግዛት፣ የርስዎን ወንበር ለመያዝ፣ ለመሰለፍ ወይም ክፍያን በተመለከተ ለመነጋገር፣ የቀዝቀት ሃሳቦችን ወይም የተሳሳተ እምነት ወደ አደባባይ ቦታዎች ሲሄዱ እርዳታ ያስፈልግዎ ይሆናል።

**ለመማር/እቅድ ለማውጣት/ለማሰብ:** የማሰብ፣ የመረዳትና የመበረታታት ችግር ካለባቸው አካለስንኩላን ጋር በተያያዘ ይሆናል። ችግርዎ የመማር፣ የማቀድና የማሰብ ችግር የሚያመጣብዎ ከሆነ ለብቻዎ በማሕበረሰቡ ለሚካሄዱት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ያስቸግርዎ ይሆናል። በሆነ ድርጊት ላይ ሲሄዱ የሆነ ነገር ሲገዙ ገንዘብዎን ለመቆጣጠር፣ የት እንዳሉ ለማስታወስ ወይም ምን እንደሚያደርጉ የሚያሳውቅ  የአብሮ ተጓዥ እርዳታ እንደሚያስፈልግዎ ይሆናል።

**ለመዘዋወር;** ከቤት መውጣት ወይም በአካባቢ መዘዋወር ማለት ነው። የአካልስንኩልነትዎ ለመዘዋወር የሚያስቸግርዎ ከሆነ ከአብሮ ተጓዥ እርዳታ ሲያስፈልግዎ በተሽከርካሪ ወንበር/ወሐጕጕልሒረ ላይ ሆኖ መዞርን፣ መመሪያዎችን በማሳየት፣ ወይም ወደ ሽንት ቤት ወይም መዝናኛ ቦታ ወዘተ. መንገዶችን ለማሳየት ይሆናል። እንዲሁም በማሕበረሰቡ ውስጥ ስለሚፈሩና፣ ጭንቀት ስላለብዎ ወዘተ. የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ያስፈልግ ይሆናል።

**እራስን ለመንከባከብ** እራስን መንከባከብ ማለት በየቀኑ ግለሰብን ለመንከባከብ የሚደረግ ሥራ ማለት እንደ የራስን ደህንነት መጠበቅ ይሆናል። ችግርዎ የርስዎን ደህንነት የሚነካ ከሆነ የአብሮ ተጓዥ እንዲያለብስዎ፣ ሽንት ቤት እንዲወስድዎ፣ እንዲመግብዎ፣ መድሃኒት እንዲወስዱ ወይም ከአደጋ እንዲከላከልዎ እርዳታ ያስፈልግዎታል።

## የአመለካች/ አሳዳጊ/ የወኪል መግለጫ

የርስዎን ማመልከቻ በተመለከተ ሊረዳ የሚችል ከርስዎ፣ ከጤና ባለሙያ ወይም አገልግሎት አቅራቢ ካለ እንዲነግሩ ይጠየቃሉ።

እርስዎ ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎ/ ወኪል በማመልከቻ ቅጹ ላይ መፈረም ይኖርበታል። የርስዎ ፊርማ የሚያመለክተው:

- በካርድ ያዡ ስያሜና ሁኔታ ላይ ተረድተው እንደተቀበሉ ይሆናል።
- ያለ አብሮ ተጓዥ እረዳት በማሕበረሰብ እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ እንደማይችሉ።
- የማመልከቻ ቅጹን መሙላት Companion Card ካርድን ለማግኘት የማያረጋግጥ ለመሆኑ እንደተረዳዎ።
- በማመልከቻ ቅጹ ላይ ያለውን መረጃ ግልፅ ለማድረግ በ Companion Card ካርድ ፕሮግራም ወይም ወኪላቸው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት መስማማትዎን።
- በቅጹ ላይ የቀረበው መረጃ ትክክለኛ ለመሆኑ ለማስረዳት ይሆናል።
- በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የቀረበው መረጃ ውሸት ከሆነ እንደሚያስቀጣ እንደተረዳዎ ይሆናል።

እንዲሁም ለወደፊት በCompanion Card ካርድ ፕሮግራም ለሚካሄደው ግምገማ ተካፋይ ለመሆን ከተስማሙ ይጠየቃሉ።

## ሙያዊ አገላለፅ

**በማመልከቻ ቅጹ ላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ የተለየ አንድ አገልግሎት ወይም እርዳታዎች የሚያገኙ ከሆነ የፕሮግራሙ/ የአገልገሎቱ ተወካይ በማመልከቻ ቅጹና ፎቶግራፎች ላይ መፈረም ይኖርበታል።**

**በማመልከቻ ቅጹ ላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ የተለየ አንድ አገልግሎት ወይም እርዳታዎች የማያገኙ ከሆነ የጤና ባለሙያ በማመልከቻ ቅጹና ፎቶግራፎች ላይ መፈረም ይኖርበታል።**

በማመልከቻ ቅጹና በፎቶግራፎች ላይ መፈረም የሚችሉ የጤና ባለሙያዎች የሚከተለውን ያካተተ ይሆናል:

- በሕክምና አሰራር የተመዘገበ
- በነርስ የተመዘገበ (ክፍል 1, 3 ወይም 4)
- ሰውነት በመነካካት ሕክምና የተመዘገበ/ Physiotherapist
- በስነ-ልቦና ሕክምና የተመዘገበ/Psychologist
- በችሎታ የታወቀ ወጌሻ ሐኪም/Qualified Occupational Therapist
- በችሎታ የታወቀ ማሕበራዊ ሰራተኛ/Qualified Social Worker
- በችሎታ የታወቀ የንግግር ሐኪም/Qualified Speech Pathologist



## ካርዱን ለያዘ ስያሜና ሁኔታዎች

1. ካርዱን የያዙ ሰዎች ወደ እንቅስቃሴ ቦታ በሚሳተፉበት ጊዜ የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ያስፈልጋል ብለው ከወሰኑ ብቻ የአብሮ ተጓዥ ካርዱ ይሰጣል።

2. በCompanion Card ካርዱ ፎቶግራፉና ዝርዝር ያለ ሰው ብቻ ካርዱን መጠቀም ይችላል።

3. Companion Card ካርድ ያላቸው ሰዎች ካርዱን ሳያሳዩ የአብሮ ተጓዝ ትኬት አይሰጥም።

4. Companion Card ካርድ ያላቸው ሰዎች በእንቅስቃሴ ቦታ ለመሳተፍ ሲመዘገቡ ወይም የራሳቸውን ትኬት ሲገዙ ለአስተባባሪው ለአብሮ ተጓዝ እርዳታ ትኬት እንደሚያስፈልጋቸው መናገር አለባቸው።

5. Companion Card ካርዱን መቀበል ማለት በእንቅስቃሴ ቦታው ለመግባት ያስችላል ማለት አይደለም። ካርዱ ያላቸው ሰዎች ትኬት ከማዘጋጀታቸው በፊት ከእንቅስቃሴ ቦታ አስተባባሪ ጋር ማረጋገጥ ነው።

6. በCompanion Card ካርድ ተሳታፊዎች የሚጠበቀው ቢያንስ በነፃ አንድ ትኬት ወይም የመግቢያ ፈቃድ ካርዱን ለያዙ ማግኘት ይሆናል። የመግቢያ ዋጋ ሁሉ በዚህ ትኬት ሊታለፍ ይችላል።

7. ካርዱ ያለው ሰው ከአንድ በላይ የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ካስፈለገው አስቀድሞ ከእንቅስቃሴ አስተባባሪው ጋር መነጋገር ያስፈልጋል።

8. በእንቅስቃሴ ቦታ አስተባባሪዎች ለሚካሄድ ማንኛውም ፕሮግራም፣ አገልግሎትና ትምህርት የአብሮ ተጓዥ ትኬት ለማግኘት ካርዱ ሊጠቀም ይችላል። ይህ የመደበኛ የመግቢያ ፍቃድ ግኝትና ሁኔታን ይመለከታል።

9. Companion Card ካርድ ከሌላ ተቀባይነት ካለቸው የቅናሽ ዋጋ ካርዶች ጋር በቅንጅት ሊያገለግል ይችላል።

10. ካርዱ ያላቸው ሰዎች በቴሌፎን ቦታ ሲይዙ የአብሮ ተጓዥ ካርዳቸውን ዝርዝር ማቅረብና ትኬት በሚወስዱበት ጊዜና በእንቅስቃሴ ላይ እያሉ ሲጠየቁ ማሳየት ይኖርባቸዋል። ካርዱን ካላሳዩ ለአብሮ ተጓዥ ትኬት ይከፍሉ ይሆናል።

11. ተባባሪ የእንቅስቃሴ ቦታዎች ካርዱ ያላቸው ሰዎች ከአብሮ ተጓዥ ጋር አብረው መሆን እንዳለባቸው ያረጋግጣል። አብሮ ተጓዡ ከካርድ ያዡ ሰው አጠገብ በመሆን እርዳታ ሲያስፈልግ መስጠት ይሆናል። የተለየ መቀመጫ ለሚያስፈልጋቸው ለእንቅስቃሴ ቦታ አስተባባሪ በወቀቱ መነገር አለበት።

12. አንዳንድ የእንቅስቃሴ ቦታ አስተባባሪዎች ለተሳታፎና ለአጠቃላይ የአስተደደር ዋጋ ያስከፍላሉ (ለምሳሌ በ fun park/መናፈሻ ከመግቢያ ክፍያ በተጨማሪ ለመጋለብ/መንዳት ክፍያ ይኖራል) ካርዱን የያዘ ሰው በተባባሪ የእንቅስቃሴ ቦታዎች ለመሳተፍ የአብሮ ተጓዥ እርዳታ ያስፈልጋል ካሉ ትኬት ሲፈቀድላቸው ይህ ለማስገባትና ለተጨማሪ ክፍያ እንደ መንዳት ወዘተ. ያካተተ ይሆናል።

13. በCompanion Card ካርድ በመጠቀም በጀምላ መግዛት ሲቻል ካርዱ ያለው ሰው የመግቢያ ዋጋ ከሌሎች ነገሮች ጋር በማጣመር እንደ ምግብ ወዘተ. የመሳሰሉትን መግዛት ይችላል። ካርዱ ያላቸው በጀምላ ለመግዛት ሲደራደሩ በእንቅስቃሴ ቦታ አስተባባሪው በአብሮ ተጓዥ ትኬት ላይ ምን እንደሚያካትት መጠራት አለበት። በCompanion Ticket ትኬት ላይ ሌሎች ግዥዎች ካልተካተቱ ካርዱን ለያዘ ሰው እርዳታው እንዳይሰናከል ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል (ለምሳሌ ምግብ ካልተካተተ፤ አብሮ ተጓዡ እንዲያመጣ ወይም ካርዱን ለያዘ ሰው ያለማቋረጥ መርዳት እንዲችል ምግብ የሚያገኝበትን መንገድ መፍጠር)።

14. ለCompanion Ticket ትኬቶች ቦታ መያዝና ትኬት የማሰራጨት ተግባር ከተባባሪ የእንክስቃሴ ቦታ መደበኛ የትኬት አሰራር ሲወዳደር ከባድ አይደለም።

15. ለእንቅስቃሴ ቦታ አስተባባሪ የቀረበው Companion Card ካርድ ትክክለኛ ለመሆኑ ከተጠራጠረ ይህንን ለCompanion Card ካርድ ፕሮግራም ሪፖርት ማድረግ አለበት። ካርዱ ያለአግባብ መሆኑ ከተረጋገጠ የአብሮ ተጓዥ ካርዱ ይሰረዛል እንዲሁም እንደገና ለማመልከትም አይፈቀድላቸውም።

16. ለCompanion Card ካርድ ማመልከቻ ሲያስገቡ የተጠቀሰውን የካረድ ባለቤት ስያሜና ሁኔታ እንደተቀበሉ ግልፅ ነው።

## ተጨማሪ ምንጮች

ስሌሎች የአካለ ስንኩል አገልግሎት ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት

**የአካለ ስንኩል በዌብሳይት መስመር ማየት**

www.disability.vic.gov.au

**Yellow Pages (ዋይት ፔጅስ)**
'ለአካለ ስንኩል አገልግሎትና እርዳታ ድርጅት' የሚለውን በዋይት ፔጅስ ላይ መመልከት።

**Department of Human Services** (በሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያ) የተቀባይና ሰ ቡድን ስለ ማህበረሰብ እርዳታና አገልግሎትባካባቢ ላሉ ለአካለ ስንኩላን፣ ቤተሰብ ለሆኑና እንክብካቤ ሰዎች ያቀርባሉ። በቴሌፎን 1800783 783 ማናገር.

በአካለ ስንኩል ላይ አድልዎ መፍጠርና ስለ መብትዎ በበለጠ መረጃ ለማግኘት

በመስተዳድሩና በፌዴራል ህጎች መሠረት አድልዎ መፍጠር ህገወጥ እንደሆነ ነው። በርስዎ ላይ አድልዎ ተፈጽሟል ብለው ካመኑ በበለጠ ማብራሪያና ምክር ከሚከተሉት ምንጮች ማግኘት ይችላሉ፤

**Victorian Legal Aid** (የቪክቶሪያ ህጋዊ እረዳታ) በነፃ ህጋዊ የሆነ ምክር በመስጠትና በህጋዊ እርዳታ የሚፈቀድልዎ ከሆነ በፍርድ ቤት ሊወክልዎ ይችላል።

በቴሌፎን (03) 9269 0234 (ከተማ ክልል)
ወይም1800 677 402 (ለገጠር ተጠቃሚ)

**Local community legal centres** (የአካባቢ ማህበረሰብ ህጋዊ የሆነ ማእከል) በነፃ ህጋዊ የሆነ ምክርና እርዳታ ያከርባል። የፌደራል ማህበረሰብ ህጋዊ የሆነ ማእከልን በማናገር በአቅራቢያዎ ባለ ህጋዊ ማእከል ማወቅ ይቻላል:
በቴሌፎን (03) 9602 4949 ያናግሩ።

**Disability Discrimination Legal Service** (አድልዎ ለደረሰበት አካለስንኩል ህጋዊ ማእከል) የማህበረሰብ ህጋዊ የሆነ አገልግሎት ሲሆን አድልዎ ለደረሰባቸው አካለ ስንኩል ህግና የነፃ መረጃ፣ ምክርና አገልግሎት በተለየ ሁኔታ ያቀርባል።

በቴሌፎን (03) 9602 4877 (በተቀዳ ድምፅ) ወይም
03 9602 4135 (TTY) ወይም
በኢሜል: **info@ddls.org.au**

**Villamanta Legal Service** (ቪላማንታ ህጋዊ የሆነ አገልግሎት) ለማህበረሰብ ህጋዊ የሆነ አገልግሎት ሲሆን ከአካለስንኩል በተያያዘ ህጋዊ የሆነ ጉዳይ በነፃ መረጃና ምክር ያቀርባል።

በቴሌፎን 1800 014 111 (በቪክቶሪያ ውስጥ በነፃ ለመደወል)

**Equal Opportunity Commission Victoria (EOCV) (በቪክቶሪያ የእኩልነት እድል መብት አስጠባቂ ኮሚሽን)**

EOCV ስለ እኩልነት እድል መብትና ሃላፊነት በምክር ማቅረቢያ መስመር በኩል በማቅረብ ሰዎች ህገወጥ የሆነ አድልዎና በደል ሲደርስባቸው ክሱን/ቅሬታውን በአስታራቂ አገልግሎት በከል መፍትሄ ለማግኘት ይረዳል። እነዚህ አገልግሎቶች አድልዎ በሌለበት፤ ሚስጢራዊና በነፃ ይቀርባል።

በቴሌፎን: (03) 9281 7111
በነፃ ለመደወል: 1800 134 142
TTY: (03) 9281 7110
ፋክስ ቁጥር: (03) 9281 7171
በዌብሳይት: www.eoc.vic.gov.au
በኢሜል: eoc@vicnet.net.au



**Human Rights and Equal Opportunity Commission (ሰብዓዊ መብትና የእኩልነት እድል አስጠባቂ ኮሚሽን)**

በሰብዓዊ ምብቶች ትምህርት መስጠት የኮሚሽኑ ዋና ሃለፊነት ሲሆን የሚቀርቡትን ቅሬታዎች መርምሮ በማጣራት ስለሰብዓዊ መብቶችና በፀረ-አድልዎ ህግ መጣስ በኩል ለቀረበው ክስ መፍትሄ ለማግኘት ይጥራል።

በቴሌፎን: (02) 9284 9600
በዌብሳይት: www.humanrights.gov.au
ለአጠቃላይ ጥያቄና የፅሁፍ ወረቀት ለማግኘት:
1300 369 711
TTY: 1800 620 241
Facsimile: (02) 9284 9611
ለክስ/ቅሬታ መረጃ መስመር: 1300 656 419 ወይም
complaintsinfo@humanrights.gov.au




## Privacy (ለብቻነት)

በCompanion Card ፕሮግራም ላይ የሚቀርበው መረጃ እንደሚመዘገብና በፋይል ውስጥ በመያዝ Companion Card ፕሮግራምን ለአስተዳደር ጉዳይና ስምምነት ከተሰጠ ለግምገማ ጉዳይ ብቻ እንደሚውል ነው።

ከCompanion Card ፕሮግራም ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሌለው ቀሳቁስ እንደማይላክልዎ ነው። የሚሰጠው መረጃ ለሌላ አይነገርም፣ አይጠቀምም በአስተዳደሩ፣ በአሰራር ወይም ግምገማ ፕሮግራም ውስጥ ተሳትፎ ለሌለው ማንም ሰው አይሰጥም። የተሰበሰበው መረጃ በነፃነት የመረጃ መጠየቂያ በከል ሊቀርብ ይችላል።

በInformation Privacy Act 2000 (Vic), the Health Records Act 2001 (Vic) እንዲሁም በሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያ የብቸኝነት ፍልስፍና መረጃ መሰረት የቀረበው መረጃዎች ይስተናገዳሉ።።።

ስለ ብቸኝነት በበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት በሚከተለው ማግኘት ይችላሉ:

- The Department of Human Services
  www.dhs.vic.gov.au/privacy
- The Health Services Commissioner
  www.health.vic.gov.au/hsc/
- The Privacy Commissioner for Victoria
  www.privacy.vic.gov.au



Companion™ card.org.au

www.companioncard.org.au